# «እረፍት አድርግ አሁን»[1]



(ለፖፕ ሙዚቃ ንጉሥ - ለማይክል ጃክሰን መታሰቢያ)



በድምጽህ ቅላፄ ዓለምን ያስደመምክ፣
በእስክስታ . . . በዳንስህ አሕዛብ ያስጨፈርክ፣
የምዕተ-ዓመቱ ሰው፤ ልቀህ የተተኮስክ፣
ያለምን ዕይታ በበጎ የለወጥክ. . . ፤
የጥበብ ማጎደር.. የሙዚቃ ድግስ፣
ማይክል ጃክሰን! የ«ፖፕ» ሊቅ ንጉሥ!

የሕፃናት አባት ፍቅርን ለጋሹ፣
ሩህሩህ፣ ትሁት.. ሰብዕ - ደሃ አስታዋሹ፣
የኛም ባለውለታ የችግር ደራሹ፣
በ«ዊ አር ዘ ወርልድ» ሕይወትን ፈዋሹ. . .።

. . . . . . . . . .

አበሳህ ይወገድ፤ መከራህም ያክትም፡፡
ራ-ቅ ብለህ እረፍ፤ ከዚህ ከተውሳኩ...፣
ከምቀኞች ዓለም፡፡
ሂድ እስከወዲያኛው.. ከፍ በል አርያም..፣
ከምታገኝበት ሰለምና ፍትህ ለዘልዓለም ዓለም!

እዚያው መድረክ ፍጠር፤ ኪነት ቤተ-መቅደስ፣
በሰፊው ሰማይ ላይ እንደልብህ ደንስ፤
(እዚህ ዓለም የሌለ)*2 ተጫወት ሙዚቃ..
ለተፈጥሮ ጌታ፣ ለፀሐይ፣ ለጨረቃ. . .
ለራስህ - ለብቻህ.. ማንም ሳይረብሽህ. . .
በፀጥታው ሕዋ እረፍት አድርግ በቃ!!

ጌታቸው አበራ
ሰኔ ፪ሺ፩ ዓ/ም
(ጁን 2009)

---

*1፣2 መንገድ ስጡኝ ሰፊ ከሚለው የግጥም መድበሉ፣ ከሠዓሊና ገጣሚ ገብረ ክርስቶስ ደስታ የተዋስኳቸው ናቸው።

---

"Please click on the link below and listen to the historical song **"We Are The World"** organized by **(USA AFRICA),** a group of noted artists, among others, the late Michael Jackson, in solidarity with the people of Ethiopia who in the 1980s suffered terrible draught, hunger, and the death of millions. May God have mercy on his soul!"

Here is the link:

**http://www.youtube.com/watch?v=WmxT21uFRwM**